# ዕቃዎች በዋስትና ስለሚለቀቁበት ሁኔታ የወጣ የአፈፃፀም መመሪያ

የኢትዮጵያ ገቢዎች ጉምሩክ ባለሥልጣን
ጥር 2002
አዲስ አበባ

# <u>ዕቃዎች በዋስትና ስለሚለቀቁበት ሁኔታ የወጣ የአፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 37/2002</u>

ዕቃዎች በዋስትና የሚለቀቁበትን ሁኔታ፣ የሚያዙ የዋስትና ዓይነቶች እና ዋስትናው ቀሪ የሚሆንበትን ጊዜ በዝርዝር የሚገልፅ የአፈፃፀም መመሪያ ማውጣት በማስፈለጉ፣

በዋስትና የሚለቀቁ እቃዎችን በተመለከተ የባለሥልጣኑ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ሁሉ ተመሣሣይና ወጥ አሠራር እንዲከተሉ ማድረግ በማስፈለጉ፣

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 በአንቀጽ 61(3) በተሰጠው ሥልጣን መሰረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## <u>ክፍል አንድ</u>
## <u>ጠቅላላ ድንጋጌዎች</u>

### 1. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ መመሪያ "እቃዎች በዋስትና ስለሚለቀቁበት ሁኔታ የወጣ የአፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 37/2002" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. <u>ትርጓሜ</u>

ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም ሲባል፡-

1. "ዋስትና" ማለት ለጉምሩክ የተገባ ግዴታ መፈፀሙን ለማረጋገጥ የሚያስችል የጥሬ ገንዘብ ተቀማጭ፣ የባንክ ጋራንቲ፣ የኢንሹራንስ ቦንድ ወይም በጽሁፍ የተደረገ የግዴታ ስምምነት ነው፡፡

2. "እቃ" ማለት ዋስትና ተይዞበት የሚለቀቅ እቃ ነው፡፡

3. **“ማጓጓዣ”** ማለት እቃዎችንና ሰዎችን የሚያጓጉዝ ማንኛውም የማጓጓዣ ዘዴ ሲሆን እንስሳትንም ይጨምራል፡፡

4. **“ሕገ ወጥ እቃ”** ማለት በባለሥልጣኑ ወይም ባለሥልጣኑ በሚያስፈጽማቸው ሕጎች የተከለከለ፣ ገደብ የተደረገበት ወይም የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ያልተፈፀመበት ዕቃ በመሆኑ ምክንያት በባለሥልጣኑ የተያዘ ዕቃ ነው፡፡

5. **“ባለቤት”** ማለት ማናቸውንም እቃ የመጠቀም፣ የመያዝ፣ ወደ ሌላ የማስተላለፍ፣ ወደ ወጭ አገር የመላክ ወይም ወደ አገር የማስገባት መብት ያለው ሰው ወይም ወኪል ነው፡፡

6. “ሰው“ ማለት የተፈጥሮ ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው::

7. **“እቃን መልቀቅ”** ማለት በጉምሩክ ቁጥጥር ሥር ያለ እቃ ለታለመለት ዓላማ እንዲውል የሚለቀቅበት ሥርዓት ነው፡፡

8. **“በመንግሥት በጀት የሚተዳደር መስሪያ ቤት”** ማለት በከፊል ወይም በሙሉ በፌዴራል ወይም በክልል መንግሥት ባለቤትነት የሚተዳደርና በጀት የሚመደብለት መስሪያ ቤት ሲሆን የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን አይጨምርም፡፡

9. **“የመንግሥት መስሪያ ቤት”** ማለት በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ በፌዴራል ወይም በክልል መንግሥት ባለቤትነት የሚተዳደር መስሪያ ቤት ነው፡፡

10. **“ዓለም አቀፍ ድርጅት“** ማለት በመንግሥታት ኅብረት የተቋቋመ ማንኛ ውም አካል ነው::

11. **“አዋጅ”** ማለት የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 ነው፡፡

12. “ባለሥልጣን” ማለት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ነው፡

## 3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በአዋጁ መሰረት ባለሥልጣኑ ዋስትና በሚጠይቅባቸው እቃዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

# ክፍል ሁለት
# ዋስትና ስለሚጠየቅበት ሁኔታ እና ስለአፈፃፀሙ

## 4. ዋስትና ስለሚጠየቅበት ሁኔታ

በአዋጁ አንቀጽ 61 በተደነገገው መሰረት የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ ባለሥልጣኑ እቃዎችን ዋስትና በመቀበል ሊለቅ ይችላል፡፡

ሀ/ የጉምሩክን ሥነ ሥርዓት ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ሰነዶች በበቂ ምክንያት ያልተሟሉ ሲሆንና እነዚህን ሰነዶች ለማሟላት ተጨማሪ ጊዜ ሲያስፈልግ፣

ለ/ ቀረጥ ሳይከፈልባቸው በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ የገቡ እቃዎች ተመልሰው መውጣታቸውን ለማረጋገጥ፣

ሐ/ ተላላፊ እቃዎች በተወሰነው መስመር ተጓጉዘው በተፈቀደ መውጫ በር ከአገር መውጣታቸውን ወይም መራገፊያቸው ወደ ሆነው የጉምሩክ ጣቢያ መድረሳቸውን ለማረጋገጥ፣

መ/ ስለቫውቸር ተጠቃሚዎች በሌላ ሕግ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የቀረጥ ነፃ ማበረታቻ ተሰጥቷቸው በገቡ ጥሬ እቃዎች ተመርተው ወደ ውጭ አገር የሚላኩ እቃዎች መውጣታቸውን ለማረጋገጥ፣

ሠ/ የወንጀል ክስ የሚቀርብባቸውና ለፍ/ቤት በማስረጃነት የሚፈለጉ ካልሆነ በስተቀር የጉምሩክን ሕግ በመተላለፍ የሚያዙ እቃዎችና ማጓጓዣዎች ጉዳይ የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ፡፡

## 5. <u>በዋስትና የሚለቀቁ ዕቃዎች አፈፃፀም</u>

1. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 ከፊደል ተራ ሉ-መ በተዘረዘሩት ሁኔታዎች ወደ አገር ለሚገቡ ዕቃዎች ባለሥልጣኑ ዋስትና እንዲቀርብባቸው ያደርጋል፡፡

2. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 (ሀ) እና (ሠ) ላይ የተገለፁት ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ አስመጪው ወይም ላኪው ወይም ባለቤቱ ዋስትና በማስያዝ ዕቃው ወይም ማጓጓዣው እንዲለቀቅለት በፅሁፍ ባለሥልጣኑን ሲጠይቅ ሊፈቀድለት ይችላል፡፡

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ ቢኖርም ራሱ ማጓጓዣው የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ያልተፈፀመበት የሆነ እንደሆነ ዋስትና በማስያዝ ሊለቀቅ አይችልም፡፡

## 6. <u>በልዩ ሁኔታ ስለሚለቀቁ ማጓጓዥዎች</u>

1. የዚህ መመሪያ አንቀጽ 5(2) ድንጋጌ ቢኖርም የተያዘው ማጓጓዣ ባለቤት፡-
   ሀ/ የመንግሥት መስሪያ ቤት፣ ወይም
   ለ/ የዓለም አቀፍ ድርጅት፣ ከሆነ ብቻ ባለሥልጣኑ ዋስትና በመቀበል ሊለቅ ይችላል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት ማጓጓዣው በዋስትና ያልተለቀቀ እንደሆነ ወይም በንዑስ አንቀፁ ከተዘረዘሩት ውጭ የሚገኙ ባለቤቶች ባለሥልጣኑ ባወጣው ሕገወጥ እቃዎችን በሚያጓጉዙ

የማጓጓዣ ባለቤቶች ላይ ስለሚወሰድ አስተዳደራዊ እርምጃ ለመወሰን በወጣው የአፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 13/2001 መሰረት እንደ አግባብነቱ ይስተናገዳሉ፡፡

## ክፍል ሶስት

## የዋስትና ዓይነት፣ መጠን፣ ዋስትናው ተመላሽ ወይም ገቢ የሚሆንበት ሁኔታ

### 7. የዋስትና ዓይነቶች

1. በአዋጁ መሰረት ባለሥልጣኑ ለሚጠይቀው ዋስትና በጥሬ ገንዘብ፣ በባንክ ዋስትና፣ በኢንሹራንስ ቦንድ ወይም በፁሑፍ በተደረገ የግዴታ ስምምነት ሊቀርብ ይችላል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ላይ የተገለፀው ቢኖርም በባለሥልጣኑ የተያዘው ማጓጓዣ የዓለም አቀፍ ድርጅት የሆነ እንደሆነ የሚቀርበው የጥሬ ገንዘብ ዋስትና ብቻ ነው፡፡

### 8. የዋስትና መጠን

1. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 በተገለጸው ምክንያት በዋስትና ለሚለቀቅ ዕቃ የሚያዘው የዋስትና መጠን ለጉምሩክ ቀረጥና ታክስ እና ለሌሎች ክፍያዎች በቂ መሆን ይኖርበታል፡፡ መጠኑ በእርግጠኛነት የማይታወቅ ከሆነ ባለሥልጣኑ በገመተው ከፍተኛ የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ እና ሌሎች ክፍያዎች መጠን ይሆናል፡፡

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አቀንጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም የዓለም አቀፍ ድርጅት ንብረት በሆነው ማጓጓዣ ላይ የተጫነው እቃ የተከለከለ ወይም ቀረጥና ታክሱ ሊወሰን የማይችል ከሆነ የሚያዘው ዋስትና በቁርጥ ብር 50,000 (አምሣ ሺህ) ይሆናል፡፡

3. የዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም በመንግሥት በጀት የሚተዳደር መስሪያ ቤት ማጓጓዣ ላይ ለተጫነው ሕገ ወጥ እቃ ዋስትና የሚሆነው በመስሪያ ቤቱ የበላይ ሃላፊ የተፈረመ የፁሑፍ ደብዳቤ ብቻ ነው፡፡

## 9. ዋስትናው ተመላሽ ወይም ቀሪ የሚሆንበት ጊዜ

1. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 ላይ በተዘረዘሩት ምክንያቶች የተያዘ ዋስትና ተመላሽ የሚሆነው፡-

   ሀ/ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ለማስፈፀም የሚያስፈልገውን ሰነድ አስመጪው ወይም ላኪው በ30/ሰላሣ/ ቀናት ውስጥ አሟልቶ ሲያቀርብ ወይም ማቅረብ ያለመቻሉን በበቂ ምክንያት አስረድቶ የሰነዱን ቅጂ ባለሥልጣኑ ሲቀበል፣

   ለ/ በጊዜያዊነት ወደ አገር የገባው ዕቃ በተፈቀደለት የጊዜ ገደብ ተመልሶ ከአገር ለመውጣቱ ማረጋገጫ ሲቀርብ፣

   ሐ/ ተላላፊ ዕቃዎች በተፈቀደው ቦታ መድረሳቸው ወይም በተፈቀደው መውጫ መውጣታቸው ሲረጋገጥ፡

   መ/ በቀረጥ ነፃ ማበረታቻ የገቡ ጥሬ እቃዎች በተፈቀደው የጊዜ ገደብ ተመርተው ወደ ወጭ አገር ለመላካቸው ማረጋገጫ ሲቀርብ፣

ሠ/ የጉምሩክን ሕግ በመተላለፍ ለተያዙ እቃዎች በፍ/ቤት ወይም በአስተዳደራዊ መንገድ የመጨረሻ ውሳኔ ሲሰጥ ነው፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት የተያዘው ዋስትና ተመላሽ ሲደረግ ወይም እንደአግባብነቱ ቀሪ ሲደረግ ለባለሥልጣኑ በሚቀርብ ጥያቄ መነሽነት ግዴታው መፈፀሙን የሚያሳይ ማስረጃ ባለሥልጣኑ መስጠት አለበት፡፡

## 10. ዋስትናንን ገቢ ስለማድረግ

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 9 ላይ በተገለፀው የጊዜ ገደብ መሠረት ዋስትናውን ተመላሽ ወይም ቀሪ የሚያደርግ ማስረጃ ካልቀረበ ዋስትናውን የፈቀደው የሥራ ሂደት ለባለሥልጣኑ ገቢ እንዲደረግ ማዘዝ ይቻላል፡፡

## ክፍል አራት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 11. ስለማመልከቻ አቀራረብና ውሣኔ አሰጣጥ

1. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5/2/መሠረት ለቅ/ጽ/ቤቶች የዋስትና ጥያቄ የሚቀርበው፡-

ሀ/ የጉምሩክን ሥነ-ሥርዓት ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ሰነዶች በበቂ ምክንያት ያልተሟሉ ሲሆንና እነዚህን ሰነዶች ለማሟላት ተጨማሪ ጊዜ ለመጠየቅ የሆነ እንደሆነ ለጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አፈፃፀም የሥራ ሂደት፣

ለ/ የጉምሩክን ሕግ በመተላለፍ የተያዙ ዕቃዎች ከሆነ ለህግ ማስከበር የሥራ ሂደት፣

ነው፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ማመልከቻ የቀረበለት የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ወይም የሕግ ማስከበር የሥራ ሂደት የዋስትናውን መጠን በመወሰን ወይም እንዲወሰን በማድረግ በተወሰነው መሠረት ዋስትናው እንዲያዝ ውሣኔ ይሰጣል፡፡

## 12. <u>የአንድነትና ነጠላ ኃላፊነት</u>

1. በዚህ መመሪያ መሠረት የባንክ ጋራንቲ ወይም የኢንሹራንስ ቦንድ የሰጠ ድርጅት በአዋጁ አንቀጽ 62(4) መሰረት ከባለዕዳው ጋር ዕዳውን ከነወለዱና ወጪውን ጭምር የመክፈል የአንድነትና የነጠላ ግዴታ አለበት፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ላይ የተገለፀው ግዴታ በዋስትና ወረቀቱ ላይ በግልፅ መስፈር ይኖርበታል፡፡

## 13. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

ይህ መመሪያ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት በተያዙ ጉዳዮች ላይ የዚህ መመሪያ ድንጋጌ ተፈፃሚ ሊሆን ይችላል፡፡

## 14. የተሻሩ መመሪያዎች

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረኑ መመሪያዎች፣ ሰርኩላሮች እና የአሰራር ሥርዓቶች በሙሉ በዚህ መመሪያ ተሽረዋል፡፡

## 15. <u>*መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ*</u>

*ይህ መመሪያ በባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ተፈርሞ ከወጣበት እለት ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡*

*አዲስ አበባ*______________*ቀን* 2002 *ዓ.ም.*

*መላኩ ፈንታ*

*የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን*

*ዋና ዳይሬክተር*